*In the loving memory of*

# MEQUANINT GEZU





## ኣቶ መኳንንት ገዙ

1957-2013

በአቶ መኳንንት ገዙ ድንገተኛ ሞት የተሰማንን
ሀዘን እንገልፃለን

አብሮ አደግ ጓደኞቹ፡
ከቤተሰብ አባላቶች
ከልጆቹ ጓደኞቹ፡
ከ27 ዕድር አባላቶች





FUNERAL AND PRAYER SERVICE
9902 Braddock Rd, Fairfax, Virginia
22032

## የአቶ መኳንንት ገዙ አጭር የህይዎት ታሪክ

አቶ መኳንንት ገዙ በ1957 ዓ.ም በበጌምድርና ስሜን ክፍለ ሀገር በጎንደር ከተማ ቀሃ እየሱስ ከአባታቸዉ ከአቶ ገዙ ደስታና ከእናታቸዉ ከወይ/ይጋርዱ አራጋዉ ተወለዱ።

ዕድሜዉ ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በመሰረተ ትምህርት ቤትና ሁለተኛ ደረጃ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማጠናቃቅ ላይ እያለ በጊዜዉ የአገሪቱ የፖለቲካ ለዉጥ ምክንያት በ1975ዓ.ም በእድገት በህብረት የዕዉቀትና የሥራ ዘመቻ በመሳተፍ ለሚወደዉ አገርና ለሚያከብረዉ ሕዝብ አስተዋፅዖ በማድረግ ግዴታዉን ተወጥተዋል።

አቶ መኳንንት ከእድገት በሕብረት ዘመቻ ከተመለሰ በኋላ የግል ጥቅም ሳያታልለዉና በጊዜዉ መሳተፍ የነበረበትን ከፍተኛ የትምህርት ዕድል በመተዉ ለሃገሬና ለህዝቤ እታገላለሁ ሁሉም ነፃ ካልወጣ በማለት በ1977 ዓ.ም በሓምሌ ወር ከአጋር ጓዶች ጋር የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲን በመቀላቀል ወደ በረሃ በመዉጣት ለተወሰኑ ዓመታት በተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች በመዘዋወር የፖለቲካ ንቃትና ትምህርት ሲያስተምር ከቆዩ በኋላ በጊዜዉ በአካባቢዉ ይንቀሳቀስ ከነበረዉ የኢሕአፓ የትጥቅ ትግል ክንፍ (ኢሕአሠን) ሠራዊት በመቀላቀል በተለያየ የድርጅቱ የትግል ሥልቶች በመሳተፍ ይህ ነዉ የማይባል ጀግንነት በማሳየት ከአጋር ጓዶቹ ጋር ተሳትፈዋል።

አቶ መኳንንት እንደ አዉሮፓዊያን አቆጣጠር በ1979 ዓ.ም ወደ ሱዳን በመሄድ ለአንድ ዓመት ከቆየ በኋላ 1981 ዓ.ም ወደ አሜሪካን አገር ሂዩስተን ቴክሳስ በመምጣት ያ ቅድሚያ ለትግሉ ነዉ ብሎ ያቋረጠዉትን ትምህርት ለመቀጠል ትምህርት ቤት በመግባት በመከታተል ላይ እያለ አሁንም እንደተለመደዉ "መጀመሪያ ቤተሰቤን መርዳትና ኑሮዋቸዉን ማሻሻል" በሚል መርህ ትምህርቱን አቋርጦ በተለያየ የሥራ ሞያ በመሰማራት ቤተሰቡን የረዳ እህት ወንድሞቻቸዉን ያሥተማረና ለቁምነገር ያበቃ ወንድም ነበር ።

አቶ መኳንንት በሂዩስተን ቴክሳስ በሚኖርበት ወቅት ከዉድ ባለቤቱ ከውይ/ሓርግ ከበደ ጋር በመተዋወቅ ለተወሰነ ጊዜ አብረዉ ከኖሩ በኋላ ወደ ቨርጂኒያ ስቴት በመምጣት ትዳር መስርተዉ ሶስት ልጆችን በጋራ አፍርተዋል ።

አቶ መኳንንት በዋሽንግተን ዲሲ የተለያዩ የመረዳጃ ማህበራትን በመመሥረትና በመምራት ከፍተኛ አስተዋጾ አድርጓል ከዚሁም ትልቁን ቦታ የያዘዉ የጎንደር ልማትና ህብረት ድርጅት ነዉ እንዲሁም ከጓደኞቹ ጋር በመሆን በሞያ ዘርፍ የተደራጀዉን አላይድ የታክሲ ኩባንያ ግንባር ቀደም በመሆን በከፍተኛ ጥረት እንዲቋቋምና ለእድግቱም ይህ ነዉ የማይባል አስተዋፅዖ አድርጓል ።

አቶ መኳንንት ለተቸገረ ደራሽ ለተራብ አጉራሽ ሰዉ በልቶ የሚጠግብ የማይመስለዉ ስለቸኝ ሳይል ዘመድ አዝማድ ሰብሳቢ መካሪና ተቆርቋሪ ለቤተሰብ ችግር በግንባር ቀደም የሚገኝ የታመመ ጠያቂና አስታማሚ ነበር ።

አቶ መኳንንት በአደረበት ህመም በህክምና ሲረዳ ቆይቶ ግንቦት 30 2013 ዓ ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየን።

ለባለቤቱ ለወ/ሮ ሓረግ ከበደ ለልጆቻቸዉ ለሩፋኤል መኳንንት፡ለዳግማዊ መኳንንት፡ለልሳኑ መኳንንትና እንዲሁም ለመላ ቤተሰባቸዉና ለወዳጅ ጓደኞቻቸዉ ቸሩ እግዚአብሔር ብርታትንና መጽናናትን ይስጥ ።

**አሜን**